# ያልተሳካው ኩዴታ

G.C 597

ኩዴታ ( coup d’etat ) የሚለው ቃል ከፈረንሳይኛ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ አናት ወይም እራስ መቁረጥን የሚያመለክት ሲሆን በቃላትነቱ ጥቅም ላይ የዋለው ግን መንግስትን በሃይል እና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ መፈንቀል ወይም ከስልጣን ማውረድን ለመግለፅ ነው።ይህ ህገ ወጥ አሰራር የታሪክ ድርሳናት ስለ መንግስታት መመዝገብ ከጀመሩበት ግዜ አንስቶ ለሺ አመታት ሲከሰት የነበረ ክስተት ነው። አብዛኛው መፈንቅለ መንግስት የሚኪያሄደው በሃይል ስለሆነ ከህብረተሰብ ክፍሉ ሃይል በቅርቡና በእጁ ያለው የወታደር ክፍሉ ወይም መሳሪያ የታጠቀው የህብረተሰብ ክፍል ነው። ለዚህም ነው ብዙ ምእት አመታት ባስቆጠረው የአለማችንን ታሪክ ብንመለከት የተደረጉት ወይም የተሞከሩት ኩዴታዎች የተካሄዱት በወታደራዊ ክፍሉ ነው። በዓለማችን ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት አብዝቶ የሚከሰትባቸው ሀገራት ያሉት በአፍሪቃ፤ በደቡብ እና በመካከለኛው አሜሪካ እንዲሁም በእስያ ሲሆን በአፍሪቃ ግን በብዛቱ ተወዳዳሪነት የለውም። መፈንቅለ መንግስት ለሃገራችንም ቢሆን አዲስ አይደለም። በኔ ህይወት ዘመን እንኳን በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት፤ በደርግ ዘመነ መንግስት እንዲሁም አሁን ስልጣን ላይ ባለው በኢህአዴግ መንግስት የመፈንቅለ መንግስት ሙከራዎች ተካሂደዋል። በአፄው ዘመነ መንግስት ብዛት ያላቸው ኩዴታዎች የተካሂያዱ ሲሆን በታህሳስ ወር 1953 ዓ ም በጄነራል መንግስቱ ነዋይና በወንድሙ በአቶ ግርማሜ ነዋይ የተካሂያደው ከፍተኛው ሲሆን በደርግ ዘመነ መንግስት ደግሞ በትልቅነቱ የሚታወቀው በከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ግንቦት 1980 ዓ ም ላይ የተካሂያደው መፈንቅለ መንግስት ነው። የኢህአዴግ መንግስትም ፓርቲው የመሰንጠቅ አደጋ ደርሶበት ነበር ያለው ከመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ውስጥ የሚጠቃለል እንደሆነ ሲነገርለት ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው መሳሪያ ሳይመዘዝ ሙከራ የተደረገና የከሸፈ መሆኑ ነው። ቀጥሎ ባለው ያልተሳካው ኩዴታ ብዬ በማቀርበው ፅሁፍ ላይ አንባቢዎቼ የትኛው መንግስትላይ የተካሂያደው ኩዴታ ይሆን ብለው እንደሚጨነቁ እገምታለሁ። ዓላማዬም አንባቢያን መላ ምት ውስጥ ለመክተት ስለሆነ ጥቂት ደቂቃዎች ግር ይል ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። ስለክስተቱ ግን ብዙ ሰው ያውቃል ብዬ አልገምትም። ከወዲሁ ግን አንባቢዎቼን ለማስገንዘብ የምወደው ታሪኩ እውነተኛ ታሪክ እንደሆነና በግዜው ቦታው ላይ የነበሩ ሰዎች አሁንም በህይወት እንዳሉ ነው። ለማንናውም ታሪኩ እነሆ፥

የድሮው አውሮፕላን ማረፊያ በዛሬው ቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ከመተካቱ በፊት በአዲስ አበባ ውስጥ አሉ ከሚባሉት ብርቅ መንደሮች አንዱ ነበር። በአካባቢው የተገነቡት መኖሪያ ቤቶች ዛሬም ቢሆን የዘመናዊነታቸው ቅርስ ግልፅ ሆኖ ይታያል። ከማይጨው አደባባይ ( አሁን ሜክሲኮ አደባባይ ) አንስቶ እስከ አውሮፕላን ማረፊያው ድረስ የነበረው አስፋልት መንገድ በአዲስ አበባ ከተማ አሉ ከሚባሉት ዘመናዊ መንገዶች አንዱ ነበር። ከመንገዱ መካከል በረድፍ ተቆፍሮ የተቀበረው አንጸባራቂ ምልክቶች ማታ ማታ መኪናዎች መስመራቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ ይረዱ ነበር። ዛሬ እንኳን ማንኛውም የአዲስ አበባ መንገድ እንደዛ ያለ ዘመናዊ የመንገድ ምልክት የለውም። ከመንገዱ ዳርና ዳር ማዝጋጃ ቤት የተከላቸው የጥድ ዛፎች ተጨማሪ ውበት አክለውበት ነበር። ዛፎቹ የተተከሉበት ፊት ለፊትያለ ቤት ለዛፎቹ እንክብካቤ ሃላፊነት ነበረበት። ከሰፈራችን ውስጥ ለአዲሶቹ ጥድ ዛፎች ወደር የማይገኝለት እንክብካቤ ሰጥተው ያሳደጉ ሰፈርተኛችን ቢኖሩ አቶ ባህታ የሚባሉ ነዋሪ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል። ሀገራችንን ለመጎብኘት የሚመጡ የሀገር መሪዎች የሚያልፉት በዚሁ ታሪካዊ መንገድ ነበር። አበበ ቢቂላ እንኳን በሮም በተካሂያደው ኦሎምፒክስ በማራቶን ውድድር አሸንፎ ለአፍሪቃና ለሀገራችን የመጀመሪያውን ወርቅ ሜዳልያ ይዞ ሲመጣ ያለፈው በዚሁ መንገድ ነበር። ሕዝቡ እንዴት ያለ ከፍተኛ ደማቅ አቀባበል እንዳደረገለት እስከዛሬ ድረስ በአዕምሮዬ አለ።

የኛ መኖሪያ ከልደታ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት የሚገኘው ሰፈር ውስጥ ነው። እንደዛሬው የቦሌ ልጆች ባንሆንም በግዜው አሪፍ መንደር ውስጥ ነዋሪዎች ስለነበርን ሰፈሬ ልደታ ነው ማለት ያኮራን ነበር። ሠፈራችን ነዋሪው በአብዛኛው ሀበሾች ብንሆንም የጣልያን ተወላጆች በብዛት ይገኛሉ። በሙሉ አባወራዎቹ ጣልያኖች ሲሆኑ ሚስቶቻቸው ግን ሁሉም ኢትዮጵያውያን ናቸው። ልጆቻቸው እንዳባቶቻቸው ነጮች ሲሆኑ አልፎ አልፎ ግን እኛን የመሳሰሉ ጠየምየም ያሉ ልጆች ይወለዳሉ። ሀሜታው ከትልልቆቹ ያልፍና እኛ ትንንሾቹ ዘንድ ይደርሳል። ለጥቋቁሮቹ ጣልያኖች የሚወጣላቸው ያው የጣልያን ስም ስለነበር ስማቸው የፈረንጅ ሆነ እያልኩ እቀና ነበር። የሰፈር ልጆች ቡድን መሪያችን ከነዚሁ የጣልየን ልጆች ውስጥ አንዱ ነበር። ለመሪነት የተመረጠው በእድሜ ትልቅ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የቆዳው ነጭነትም አስተዋፅኦ እንዳደረገ ከግዜ በህዋላ መረዳት ችያለሁ።ስሙ ቤኒቶ ይባላል። በዕድሜ ታላቃችን በመሆኑና ጉልበታምም ስለነበር መሪነቱን በገሃድ የሚቃወመው አልነበረም። ስለብዙ ነገር ከኛ ቀድሞ ዕውቀት ያለው እሱ ነው። ከእርሱ የተሻለ ሌላ ልጅ ስላልነበረ መሪነቱን ካለተቀናቃኝ ይዟል። ሌሎቹም የጣልየን ልጆች አሜን ብለው ተቀብለዋል። ሌሊቱ ሊነጋ ሰማዩ የአህያ ሆድ ሲመስል ከአልጋው ተነስቶ ወፎችን መከታተልና ማጥናት የዘወትር ልምዱ ነበር። እያንዳንዱን ወፍ ከነቤተሰቡ ያውቃል። በተለይ እስካሁን የማልረሳው «እያያስር» ብሎ ስም ያወጣለትን ከሌሎች አብልጦ የሚወደውን ወፍ ነው። ጎረቤታሞች ስለነበርን አንዳንድ ግዜ በጠዋት እነሳና አለቃዬንና ወፎቹን እቀላቀላለሁ። እያንዳንዱን ወፍ ያስተዋውቀኛል። ስም አላቸው። ለእኔ የማይታየኝን ቅርፅና ቀለማቸውን ሊያስረዳኝ ይሞክራል። የእያያስር ሚስቱንና ልጆቹን ለይቶ ያሳየኛል። ወንዱንና ሴቱን እንዴት እንደሚለይ ልደታ ትወቅ። ከሌላ ሰፈር ድንበር ገፍተው የሚመጡትን ፀጉረ ልውጥ ወፎችን ለይቶ ያውቃል። የሰፈራችን ወፎች ባላንጣ እንዳይገጥማቸው ድንጋይ እየወረወረ ይከላከላል። ከተፈጥሮ ያገኘው ስጦታ ቢሆን ነው እንጂ ከየትም እንዳልተማረው እገምት ነበር። የቀለም ምህርት እንደማይወድ

እራሱ ብዙ ግዜ ነግሮኛል። አባቱ የከባድ መኪ. ሾፌር ስለነበሩ የርሳቸውን ስራ ሊወርስ አስቦ ይሆናል እያልኩ እገምት ነበር።

ጃንሆይ ቢያንስ አንድ ግዜ በሳምንት በሰፈራችን ያልፋሉ። አንዳንድ ግዜ አልፈው ወደ ሰበታ ያቀናሉ እንጂ አብዛኛውን ግዜ ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል (የአሁኑ ጦር ሀይሎችሆስፒታል) ህሙማንን ለመጠየቅ ብቅ ይላሉ። በአብዛኛው ሐሙስ ዕለት ከሰዓት በኋላ እንደነበር አስታውሳለሁ። በዚያን ግዜ ልጆች ሆነን በዓለም ላይ ብርቅ ነገር ቢኖረን ጃንሆይና ኮንቮያቸው ( አጃቢ መኪናዎቹ) ነበሩ። የሳቸው መኪና ከልክ ያለፈ ቆንጆ ነበር።ቆንጆዎ ነበሩማለቱይሻላል።ምክንያቱም በየግዜው ይለዋወጡ ነበር። ቤኒቶ የመኪናዎቹን ስም ይነግረናል፤ለማስታወስ ግን ይከብደን ነበር። ለዕውቀቱ ወሰን የለውም ብለን ስለምናምን፤ስለምንም ነገር የምንጠይቀው እሱን ነው። ለጥያቄያችን መልስ አጥቶ አያውቅም። እኛም ለሚሰጠን መልስ አዎንታዊ ምላሽ እንጂ መከራከር ወይም መቃወም አንችልም። ሌሎቹ ጣልያኖች ጓደኞቻችንም አለቃነቱን ተቀብለው እንደኛው የሱ ጀሌ ሆነዋል። እስቲ ስለ አባባ ጃነሆይ መኪናና አጃቢዎቻቸው የማስታውሰውን ላውሳችሁ፦ የንጉሠ ነገሥቱ ኮንቮይ ቀዳሚ አስተናጋጅ፤ የሚያልፉበትን መንገድ ሥነስርዐትና መልክ የሚያስይዝ፤ የንጉሱን ያህል የሚፈራ ሞተረኛ የፖሊስ መኮንን ነበር። ፊቱን ምን ግዜም እንዳኮሳተረ፤ዐይኑን እንዳጉረጠረጠ፤ በእጁ መኪናዎች ከመንገድ ላይ እያባረረና እያስቆመ ኮንቮዩን ይመራል። ሞተር ብስክሌቱ ላይ የሚቀመጠው ለየት ባለ ሁኔታ እንደነበር አስታውሳለሁ። መቀመጫዊ እንደሚያምር ሴት ወይዘሮ ወገቡን ሰበር አድርጎ ወደኋላ ለጠጥ ብሎ ይቀመጣል። ግርማ ሞገስ የሰጠው ግን ጫፍ ጫፉ ወደላይ ተጠምዝዞ በእንክብካቤ ያሳደገው ፂሙ ነው። ሌላ እንደዚህ ዓይነት ፂም የነበራቸው ጄነራል መንግስቱ ነዋይ ነበሩ። ይህ ዝነኛ የጃነሆይ ኮንቮይ መሪ ፂሙ እንደ መለያ ተወስዶ «በቀለ ፂሞ» በመባል ይታወቅ ነበር። ከሱ ሞተር ለጥቆ አንድ ወይም ሁለት መኪና ይከተልና ከዛ ለጥቆ የጃንሆይ መኪና ይከተላል። በውበቱም ሆነ በሽንጠ ረዥምነቱ ይለያል። ከመኪናው በስተኋላ መቀመጫ ንጉሱ ይቀመጣሉ። አንዳንድ ግዜ የልጅ ልጆቻቸው አብረዋቸው ይኖራሉ፤ግና ለዐይን ብትሰወርም ምን ግዜም ከአጠገባቸው የማትጠፋው ድንክ ውሻቸው ትኖራለች። ለጥቆ ሌላ የቤተ መንግስት መኪናዎች ይከተሉና ዝነኛዎቹ የንጉሱ የክብር ዘበኞች ወይም በተለምዶ «አንጋች» እየተባሉ የሚጠሩት በሁለት ሸፍን ጂፕ መኪና ሆነው ይከተላሉ። ቁመታቸው ከ1 ሜትር ከ90 በላይ የሆነ፤ ተክለ ሰውነታቸው በጡንቻ ብቻ የፈረጠመ፤ እንቅስቃሲያቸው ፈጣን፤ አንድን ሰው ትኩር ብለው በማየት ብቻ ብርክ የሚያስይዙ፤የንጉሡ አንበሳዎችነበሩ። አንጋች ተብለው የሚጠሩት በሚያነግቱት አጭር አውቶማቲክ ጠብመንጃ ምክንያትይመስለኛል። ከነሱ ቀጥሎ ከፍተኛ የሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣናት እንዲሁም የቤተክህነት ሰው ይከተላሉ።

በሚያልፉበት መንገድ ሁሉ መኪናም ሆነ እግረኛ ባለበት ቀጥ ይላል። ሁሉም ሰው እጁንወደ ኋላ አድርጎ የንጉሱን መኪና መቃረብ ይጠብቃል። መኪናቸው ፊትለፊት ከመድርሱ በፊት 10 ሜትር ያህል ሲቀረው ከወገብ በማጎንበስ እጅ ይነሳል። አብዛኛው ሰው በጉልበቱ ተንበርክኮ መሬት ይስማል። በተለይ ሴቶቹ ዕልልታውን ያቀልጡታል። ቀና ተብሎ እንክዋን ፊታቸውን ለማየት እንፈራ ነበር። የውጭ ሀገር መሪ ተቀብለው አብረው ሆነው በሰፈራችን ሲያልፉ የሚሄዱት በግልፅ መኪናቸው ስለነበር የዛን ግዜ ነበር መልካቸውን ሳንፈራ ማየት የምንችለው። ስለተባለ ብቻ ለማለት ሳይሆን እንደርሳቸው ያለ ግርማ ሞገስ ያለው እጅግ የሚያምር ሰው እስከዛሬ አይቼ አላውቅም። ለዚህም ነው ጣልያኑ የቡድን መሪያችን ቀና ብሎ ማየት ክልክል መሆኑን ቢያስጠነቅቀንም ከተንበረከክንበት አሾልቀን ሰርቀን የምናያቸው። ቅርብ ለሆነ ጓደኛችን ብቻ በሚስጥር እንነግራለን። እኔም አይቻቸዋለሁ ካለ« ምን አይነት ልብስ ነው የለበሱት?»ብለን በመስቀልኛ ጥያቄ እናፋጥጣለን። የጃንሆይ ኮንቮይ የሚቆመው ለሶስት ነገሮች ብቻ ነበር። ለታቦት፤ ለሙሽራና ለቀብር ለሚሄድ አስከሬን። ለታቦት ከሆነ ከመኪናቸው ወርደው ቆባቸውን አውልቀው ይሳለማሉ፤ ለሙሽራ ከሆነ ከመኪናቸው ሳይወርዱ ሙሽሮችን አስጠርተው ካነጋገሩ በህዋላ የገንዘብ ስጦታ ሰጥተው ያሰናብታሉ። ሙሽሮችም አጋጣሚውን እንደ መልካም ዕድልና ገድ ቆጥረው ሽልማት የተሰጣቸውን ገንዘብ ለረጅም ግዜ ሳይጠቀሙበት እንደሚያቆዩ ይነገራል። አስከሬን ካጋጠማቸው ቆመው ያሳልፋሉ። ሌላው የውዴታ ግዴታ ሆኖ የንጉሱ መኪና የሚቆምበት ግዜ እንደነበር ትዝ ይለኛል። አቤቱታ ለማስማት የሚፈልጉ ዜጎች ይህን አቋራጭ መንገድ በመጠቀም መንገድ ዳር አድፍጠው በመጠበቅ ንጉሱን እጅ የሚነሱ መስለው መኪናቸው ፊት ለፊት ሲደርስ ነጠላቸውን ከመኪናው ፊት ይጥላሉ። የጃነሆይ ሹፌር የውስጥ የስራ መመሪያ ሳይኖረው አይቀርም፤ መኪናውን ቀጥ አድርጎ ያቆማል። ኡኡታውና አቤቱታው ይቀልጣል። ባለ አቤቱታዎቹ ወንዶች ከሆኑ አብዛኛውን ግዜ የመሬት ክርክር ጉዳይ ሲሆን ሴቶቹ ደግሞ የሙት ልጆች ማሳደግ አልቻልኩም ልጆቼን ተቀበሉኝ ይላሉ። በጣም የሚገርመው ጉዳይ ንጉሱ የማንንም አቤቱታ አልፈው አይሄዱም ነበር። የህዝብን በደል እንደዚህ አቋራጭ በሆነ መንገድ መፍትሄ ይሰጡ ነበር።
ቤኒቶና ማንኛውም የጣልያን ዜጋ ላይ ከቤታቸው እንዳይወጡ ማዕቀብ የሚጣልበት ሁኔታ ነበር። ለጉብኝት የመጣው መሪ የዩጎዝላቩ መሪ ማርሻል ቲቶ ከሆነ ማንኛውም የኢጣልያ ዜጋ እሱ በሚያልፍበት መንገድ እንዳይታይ ማስጠንቀቂያና ትዕዛዝ ይተላለፍ ነበር። የዛን ዕለት ብቻችንን ካለአለቃ እምንውልበት ቀን ነበር። ቤኒቶ በዚህ የጣልያን ዜጎች ላይ በተጣለው ማዕቀብ እኛ ያመጣንበት ይመስል ለሶስት ቀን ያህል ያኮርፈን ነበር። አመተ ምህረቱን በትክክል ባላስተውሰውም በመጀመሪያዎቹ 1950ዎቹ ላይ አንዱን ቀን የሰፈራችን ነዋሪ ቁጥር በአንድ ቁጥር ወደ ላይ ከፍ አለ።ከየት መጣ ሳይባል ከአቶ ባህታ ቤት ፊትለፊት አስፋልቱ ዳር ካለው የእግረኛ መሄጃ ላይ አንድ እብድ መኖር ጀመረ።
በመጀመሪያ የሰፈሩ ሰው በጥርጣሬ ተመልክቶት በተለያዩ መስፈርቶች ወንጀለኛ እንዳልሆነና በእርግጥ የአዕምሮ በሽተኛና ነዋሪው ላይ አደጋ የማያደርስ እንደሆነ ማረጋገጥ ነበረበት። በተለይ ልጆች ለነበርነው አጠገቡ እን ዳንደርስ በየቀኑ ማስጠንቀቂያ ይሰጠን ነበር። እየዋለ ሲያድርና አደገኛ እንዳልሆነ ሲታወቅ የሰፈሩ ሰው ፍራቻ ውን አስወግዶ እንደውም የሚበላና የሚጠጣ ይሰጠው ጀመር።አንድ ግራ ያጋባን ፀባዩ ፍጹም ዝምተኛ ነው።

ማንንም አያነጋግርም። ለእብድ ፀባይ እንግዳ ነገር ነበር።ካልተኛቁጭ ብሎ ሩቅ አሻግሮ እንደሚመለከት ሰው ዐ
ይኑን አንድ አቅጣጫ ላይ ይተክልና ለረዥም ግዜ ይቆዝማል። ወሬኛ የሚባሉት የሰፈራችን ሰዎች እንኳን ስለሱ
ለማወቅ ጥረት አድርገው የሚያወሩት አጥተው ተስፋ ቆርጠው ትተውታል።

ቤኒቶ እንዴትና ከወዴት እንዳገኘው አናውቅም የአዲሱ እብድ ስም በቀለ እንደሆነ ነገረን። ቀስ በቀስ ሁሉም
ለመደውና አንድ ቅጥያ የቅፅል ስም ተጨመረለትና«በቀለ እብዱ» እያልን መጥራት ጀመርን። ቀን ቀን መንገ
ድ ላይ ሲዞር ይውላል። ዋናውን መንገድ ተሻግሮ ወደ ፕሪሞ ወፍጮ የሚወስድው መንገድ ዳር ላይ ያለው ጉ
ልት ላይ አልፎ አልፎ ዘረፋ ያካሂዳል። የሚገርመው በአብዛኛው የሚዘርፈው በርበሬና ሚጥሚጣ መሆኑ ነው።
ሚጥሚጣውን ሳይቀር ይቅማል። «እላዩ ላይ ያለው አጋንንት እኮ ነው! አበስኩ ገበርኩ!» ይላሉ የጉልት ሴቶ
ች። ተባብረው አስፈራርተው ያባርሩታል። አመሻሽ ላይ እዛው የተለመደው ቦታው ላይ መጥቶ ይተኛል። ከአን
ድ ከቆሸሸ አንሶላ በስተቀር ብርድ ልብስ የሚባል የለውም። ልብሱም አንድ ነች፤ቅያሬ የለውም። ፀጉሩንም ስ
ለማይቆረጥና ስለማያበጥር ጨበሬ ነው። ቁመቱ መካከለኛ ሲሆን የቆዳው ቀለም ሲበዛ ጥቁር ነው።

አንድ ቀን ጠዋት አረብ ቤት(ሱቅ) ተልኬ ስመለስ በቀለ እብዱ በእጁ የሆነ ነገር ይዞ አቀርቅሯል። ምን ይሆ
ን የያዘው ብዬ ለማወቅ ካደረብኝ ጉጉት ተጠግቼ ሳይ በእጁ አሮጌ ጋዜጣ ይዞ ያነባል።ጋዜጣው ከማርጀቱ ብዛ
ት ወይቦ ቀለሙን ቀይሯል። አጠገቡ ሰው እንደቆመ ታወቀውና ቀና ብሎ ሲያይ ዐይን ለዐይን ተጋጠምን። ከዚ
ህ በፊት ያየሁት ዐይን አልነበረም። በሩቅ እያየ የሚቆዝመው የበቀለ ዐይን አልነበረም። የቁጭት፤የትዝብትና የን
ዴት ስሜት የቀላቀለ የጤነኛ ሰው ዐይኖች ነበሩ። ትኩር ብሎ ሲያየኝ ሰውነቴ ውስጥ ያለውን ደም አቀዘቀዘው
። ብርክ ያዘኝ። ተነስቶ የሚተናኮለኝ መሰለኝ። ዐይኔን ከዐይኑ ላይ ነቅዬ እግሬ አውጪኝ አልኩ። እቤቴ ስደርስ
ቃት እየተነፈስኩ በር ላይ ቆሜ ወደኋላዬ ዞሬ እንዳልተከተለኝ ማረጋገጥ ነበረብኝ። እነኛ አስፈሪ አይኖች ለረ
ዥም ግዜ ማታ ስተኛ ቅዠት ሆነው አስቸገሩኝ።

ከጥቂት ሳምንታት በህዋላ በአንደኛው ቀን ከሰዓት በህዋላ የቡድን መሪያችን ጃንሆይ ወደ ልዕልት ፀሀይ ሆስፒ
ታል ስላለፉ ሲመለሱ እንድናያቸው መንገዱ ዳር እየተጫወትን እንጠብቅ ብሎ ነገረን። ዘወትር የምንደሰትበት
ግዜ ማሳለፊያችን ስለነበር በደስታ ተቀበልነው። መንገዱ ዳር እየተጫወትን የበቀለ ፂሞን ሞተር ብስክሌት ከሩ
ቁ ለማየት ወደ ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል አቅጣጫ አልፎ አልፎ እንቃኝ ነበር። የሰፈራችን ትልልቅ ሰዎችም ከ
ቤታቸው እየወጡ ሁለት ሶስት ሆነው እርስ በርስ እየተጨዋወቱ ጃንሆይን ለማየትና እጅ ለመንሳት ከኛ ጋር
ጠብቁ ጀመር። ከመንገዱ ማዶ ያሉ የኔ ብጤዎች እንኳን የልደታን ቤተ ክርስቲያን ግንብ ለቀው ወደ መንገዱ
ጠጋ ብለው እንደሌላው ወሬ ፍለጋ አቆብቅበዋል። በቀለ እብዱም የተለመደው ቦታውን ይዞ ቁጭ ብሏል። ከጎ
ኑ ቡቱቶ ጨርቆቹን ሰብስቦ አጠገቡ አድርጓል። አልፎ አልፎ ጨበሬ ፀጉሩን ይፎክታል። እንደወትሮው ስለሱ
ቁብ የሰጠውም ሰው አልነበረም። እያለ የሌለ ሰው። እሱም አቀርቅሮ አካባቢውን ይቃኛል።

እንዳይደርስ የለም ሰዓቱ ደረሰና የበቀለ ጢሞ ሞተር የህንፃ ኮሌጅ ዳገትን ጨርሶ ብቅ አለ። አዋቂ የለ ልጅ
ሁሉም የሚያድርገውን ትቶ ወደ በቀለ ጢሞ አቅጣጫ ዞረ። እንደወትሮው ጢሞ እግረኛውንም ሆነ ባለመኪና
ውን እየተቆጣ፤ በዛ በሚያስፍሩ አይኖቹ እየገላመጠ፤ በኃይለ ቃል ማስጠንቀቂያ እየሰጠ ወደ ልደታ ቤተ ክር
ስቲያን አቅጣጫ ይቃረብ ጀመር። የጃንሆይ መኪና ሲታየን እንደለመድነው እጅ ለመንሳት ተዘጋጀን። ልክ በቀለ
ጢሞ እንዳለፈ፤ በቀለ እብዱ ከተቀመጠበት ድንገት ብድግ አለ። በሃሳቤ ዛሬስ ህመሙ ተሻለው መሰል ጃንሆ
ይን እጅ ሊነሳ ነው ብዬ አሰብኩ። አይኔ ግን ጃንሆይን ትቶ እሱ ላይ ተሰክቶ ቀረ። ከዛች ሰከንድ ጀምሮ ያለ
ው ሂደት እንደ ህልም እንጂ በእውን የማየው ሊመስለኝ አልቻለም። በቀለ በቀኝ እጁ ትልቅ ድንጋይ ይዟል።
ጎኑ ከነበረው ቡትቶ ጨርቅ ውስጥ ደብቆት ነበር ማለት ነው። ከቆመበት ወደፊት በፍጥነት ወደ ጃንሆይ መኪ
ና ተራመደና የያዘውን ድንጋይ ለመወርወር ተንጠራራ። ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ ድንጋዩን ጃንሆይ መኪና ላ
ይ ወረወረ። ይህ ሁሉ የሚታየኝ በቀስታ እንደሚንቀሳቀስ ፊልም አይነት ነበር። የወረወረው ድንጋይ ከንጉሱ መ
ኪና ላይ ሲያርፍ የፈጠረው ድምፅ የተተኮሰ ጥይት ጩኸት ያህል ነበር ። እጅ ለመንሳት ገና ከጉልበቴ ሸብረክ
እንዳልኩ ነበር ይህ የማይታመን ጉድ የተፈጠረው። እንደዛው ባለሁበት ሁኔታ በድኔ ድርጊቱን ይከታላል። የጃነ
ሆይ ሾፌር መኪናውን አላቆመም፤ጉዞውን ፈጠን አድርጎ ቀጠለ። በቀለ ፂሞም ከበስተኋላ ምን እንደተፈጠረ
ማወቁን ልደታ ትወቅ ቁልቁለቱን ይዞ ነጎደ።

ቀድሞ አጎንብሶ የነበረው ሰው ሁሉ የተወረወረው ድንጋይ የፈጠረውን ጩህት ሲሰማ ተደናግጦ ቀና ሲል
የንጉሱ መኪና ካለወትሮው በፍጥነት አልፏል። ከህዋላ በጂፕ መኪና የሚከተሉት አንጋቾች ያሉበት መኪና ሳይ
ቆም የህዋላውን በር ከፍተው እየዘለሉ ወረዱ። በቀለ እብዱ ካስቀመጠው ቀሪ ድንጋዮች ደግሞ ሊያነሳ ይመስ
ለኛል ወደ ቦታው ሲሮጥ አንጋቾች ደርሰው ያዙት። ዕሳት ለብሰው ዕሳት ጎርሰዋል። ቀድሞ የያዘው አንጋች በ
ሰደፍ እራሱን ሲመታው ከእግሩ ወዲያው ሸብረክ ብሎ መሬት ከመንካቱ በፊት ሌሎቹ አንከብክበው አንስተው
እንደ ጨርቅ ኳስ ወደ ሰማይ አጎኑት። መሬት እግሩን ሳያስነኩ አየር ላይ ሰደፍና ጡጫ ያወረዱበት ጀመር።
ሁሉም ሰው በድንጋጤ ደንዝዞ አፉን ከፍቶ ዐይኑን አፍጦ ይመለከታል። ድንገት ከሰፈራችን ትላልቅ ሰዎች መ
ሃል አንዱ ከመሃል ፈትለክ ብለው ወጥተው ወደ ቤታቸው አቅጣጫ ሲሮጡ ከያዘን አፍዝ አደንግዝ ተላቀቅን
ና እግሬ አውጭኝ እያልን ወደቤታችን መፈርጠጡን ተያያዝነው። ወንድሜ አጠገቤ መኖሩን ብቻ ነው ለአፍታ

ያረጋገጥኩት። የህልም እሩጫ ሆነብኝ። እግሬ አልታዘዝ አለኝ። ከአሁን አሁን ከህዋላችን ተኩስ ነበር የምጠ
ብቀው። የበቀለ እብዱን ጉዳይ ሲጨርሱ የሚያተኩሩት ወደ ሰፈሩ ሰው ነው ብዬ ፈራሁ። ማን እርዳታ ይጠየ
ቃል? በጀመሪያ እራስን ማዳን ሆነ የሁሉም አላማ። ትላልቆቹ እንኳን ወደህዋላቸው አንዴም ዞር ብለው አላዩ
ም። እኔና ታላቅ ወንድሜ እንደምንም ቤታችን ደርሰን በፍርሃት እየተርበደበድን እቤት ስንገባ ሁኔታችን እንግ
ዳ የሆነባት እናቴ «ምንድነው? ምን ተፈጠረ? እያለች በጥያቄ አፋጠጠችን። «በቀለ እብዱ» ብለን በአን
ላይ ጮህን። ስንሮጥ የመጣነው እሱ እያባረረን መስሏታል። «የጃንሆይን መኪና በድንጋይ መታ» ብሎ ወንድ
ሜ መርዶውን አረዳት። «ውይ! ልደትዬ! » ብላ ጮሃ ስታበቃ በሩን ተንደርድራ ጥርቅም አድርጋ ዘጋችው።
ክፍት የነበረውንም መስኮት እንዲሁ። ጭለማ ውስጥ ቁጭ አልን።« አይ ልደትዬ ምን አደረኩሽ? በምን ቀን
ፈረድሽብኝ» ማለቱን ተያያዘችው። ሽንቴን እንደጉድ ወጠረኝ። «ሽንቴ መጣ» አልኩ በለሆሳስ። «ምን አባክ
ላድርግልህ» አለችኝ ከጨለማው ውስጥ።ድንጋጤውና ጭንቀቱ ሊገድላት ነው። ለማልቀስ ምክንያት ነበር የምፍል
ገው፤ ማልቀስ ጀመርኩ። በዚያን ዘመን ቤት ውስጥ ያለ ሽንት ቤት ተሰምቶም አያውቅም።ከቤት ውጭ ለጋራ
በተሰራ ሽንት ቤት ነበር ያምንጠቀመው። ሁሉም ሰው ቤት ለሌሊት መጠባበቂያ የሚሆን ፖፖ ከአልጋ ስር አ
ይጠፋም። ጥቅም ላይ ከዋለ ሲነጋ ከቤት ይወጣና ታጥቦ ከበር ውጭ እንዲደርቅና እንዲናፈስ ይቀመጣል። «ፖ
ፖውን ፈልግና ሽና» አለችኝ ጨክና የማትጨክነው እናቴ። ስሸና ፊኛዬን ብቻ ሳይሆን ጭንቀቴንም ነበር የተቃለ
ለልኝ። ትንሽ ቆይቶ ከውጭ የሰዎች ድምፅ መስማት ሲጀምር በከፍተኛ ጥንቃቄ እናቴ ቀስ ብላ በሩን ከፍታ
ወጣች። እኛም ተከትለን ብቅ ስንል በሙሉ የጎረቤት ሰው ተኮልኩሏል። ሁሉም በአንድ ላይ ያወራል። የሚደማ
መጥ የለም። ርዕሱ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት በቀለ እብዱ ስላደረሰው እማይታመን ታላቅ ወንጀል ነበር። ከልጆ
ቹ መካከል ቤኒቶን ሳየው ወደእርሱ አመራሁ። አጠገቡ ሄጄ ስቆም ፊቱን ወደ እኔ ሳያዞር
« አይቼው መጣሁ » አለኝ። ስሙን መጥራት እንዳልፈለገ ሁሉ።
« እስቲ ልደታን በል» አልኩት እጄን ዘርግቼ። የተዘረጋውን መዳፌን በመዳፉ መታና
« ልደታን!» አለኝ።
ትኩር ብዬ በዝምታ ዐይን ዐይኑን ሳየው የሚቀጥለው ጥያቄዬ ምን እንደሆነ ገምቶ
« እዛው ቦታ ጥለውት ነው የሄዱት፤ ደም በደም ሆኗል፤ግን ገና ነፍሱ አልወጣችም» አለኝ። የሰፈሩ ሰው
እየጮኀ ማውራቱን ቀጥሏል። ደም በደም፤ ነፍስ መውጣት፤ የሚሉት አረፍተ ነገሮች ፍርሃቴን እንደገና ቀሰቀሱ
ብኝ። እንዴት ይሆን መሽቶ የሚነጋው። አያንዳንዱ የሰፈራችን ሰዎች ቀደም ሲል እብዱን ይጠረጥሩት እንደነበ
ር ፤ውቃቢያቸው እንዳልወደደውና ሌላም የተለያየ መላ ምታቸውን ማውራታቸውን ቀጠሉ። አንድ አዛውንት ድ
ምፃቸውን ከፍ አድርገው የተናገሩት ግን የማጠቃለያ ንግግር ነበር።
«ስሙኝ አንድ ግዜ፤ ይህ እኩይ ተግባር በቀላሉ የሚታይ ነገር እንዳይመስላችሁ። መንግስትም እንደዋዛ የሚያ
ልፈው አይደለም። ብዙ ክትትልና ምርመራ የሚደረግበት ጉዳይ ነው። ነጭ ለባሾችም ሰፈሩን ከበውታል። ሁኒታ
ው በአባዲና እየተመረመረ ነው።እንግዲህ ልደታ ትጨመርበት» ብለው ንግግራቸውን ሲጨርሱ በሚያስፈራ ፀጥ
ታ ተዋጥን። ያ ሁሉ ጫጫታ ጠፋና በሰፈራችን ውሾች ጩኀት ተተካ።«አትገቡም ወደ ቤት» ብላ እናታችን
ስትጮህ ደንብረን ሮጠን ወደ ቤት ገባን። ሁሉም ቤቱ ገብቶ ተከተተ። እየመሸ ሄደ። ምነው አባቴ ቶሎ በመ
ጣ ብዬ ተመኘሁ።

አመሻሹ ላይ እቤት ውስጥ በዝምታ ተፋጠን እያለን አባቴ ከውጭ በር አንኳክቶ ከፍቶ ገባ። ተነስቼ እንደል
ማዴ ኮቱን ተቀበልኩትና የዘወትር መቀመጫው ወደ ሆነችው የድንክ አልጋ ሄዶ ተቀመጠ። ወንድሜ ጫማውን
ካወለቀለት በህዋላ «ምነው ዝም አለችሁ?» ብሎ እናቴን ሲጠይቃት የቀኑን ጉድ ልታወራለት ስትጀምር፤ «ሰ
ምቻለሁ» ብሎ አቋረጣት። አባቴ የግዜው ጉዱ ካሳ ነበር። አብረውት የሚያመሹትም ጓደኞቹ የሱው መሰል ስ
ለነበሩ ንግግራቸው ለአብዛኛው ሰፈርተኛ አይጥምም። ከመቸው መረጃውን እንዳገኙ አይታወቅም በቀለ እብዱን
ተልእኮ የነበረው አውቆ አበድ እንደነበረና አብረውት አድማ ውስጥ የነበሩ ትልልቅ ባለስልጣናትም እዬተያዙ
እንደሆነ ነገረን። ብዙው ልጅ ፊት የማይነገር ነው ካለ በኋላ እራት አቅርቡ ብሎ እራታችን በልተን በግዜ አል
ጋችን ውስጥ ገባን። ሌሊቱ በቅዠት አለፈ።

በበነጋታው ማንም ልጅ ወደ ዋናው መንገድ ብቅ እንዳይል ማእቀብ ተጣለ። ከቤታችን በራፍ ፎቀቅ ማለት አል
ቻልንም።ትላልቆቹ እንኳን ስራ ከሚሄዱት በስተቀር ወደ ዋናው መንገድ ዝር የሚል ጠፋ። አባቴም ማታ ያወ
ራውን እናቴ አፋጣ ስትይዘው በፍፁም አላልኩም ብሎ ፋይሉን ዘጋ። ከምሳ በኋላ ቤኒቶ ሰብስቦን ያገኘውን
ዜና አካፈለን። በቀለ እብዱ እዛው ጥለውት የሄዱበት ቦታ ላይ እያቃሰተ እንደቆየና እኩለ ሌሊት ላይ ፀጥ እ
ንዳለ፤ ከዛም በጠዋት ማዘጋጃ ቤት መጥቶ ሬሳውን እንደወሰደ ልደታ ቤተክርስቲያን ግንብ ስር የሚኖሩት ለማ
ኞች እንደተናገሩ ነገረን። ሃዘንም ደስታም አልተሰማኝም። ያለፈው 24 ሰዓት ትዕይንት የልጅ አዕምሮ ከሚችለ
ው በላይ ነበር። እያደር ሲሄድ የበቀለ እብዱ ነገር እየተረሳ ሄደ። ረስተነው ሳይሆን ማስታወስ አለመፈለግም
ጭምር ይመስለኛል። ጃንሆይም በየሳምንቱ አንዱን ቀን በሰፈራችን ማለፉን ሳያስተጓጉሉ ቀጠሉ። ወደ ዋናው
መንገድ መውጣት እንደጀመርን በቀለ ይቀመጥማት የነበረች ቦታ አካባቢ ሄጄ ሲያነባት የነበረችውን ቁራጭ ጋ
ዜጣ ድንገት አገኛት ይሆን ብዬ ፈለግሁ። የለችም። የበቀለ ሚስጥር መክፈቻ ቁልፍ እዛ ላይ እንደሚገኝ እስከ
ዛሬ አስባለሁ።

በቀለ ማን ይሆን? ዕውነት አዕምሮውን የሳተ እብድ ወይንስ በደል የደረሰበት ዜጋ? ወይንስ አባቴና ጓደኞቹ እንደፈረጁት ተልዕኮ የነበረው ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ? እስከዛሬ ፍችውን ያላገኘሁለት እንቆቅልሽ ሆኖብኝ ይኖራል።

G.C. 597

የግርጌ ማስታወሻ

ከአንድ አመት በህዋላ የቤኒቶ ቤተሰቦች ሰፈራችንን ለቀው ሄዱ። አለቃችን ሳያደራጀንና እዙን በስርአት ሳያስረክብ በመሄዱ ትንሽ ግራ ብንጋባም ከጥቂት ቀናት በህዋላ ወደድሮው አደረጃጀታችን ተመለስን። ወንድሜ አጠቃሎ እዙን ባይዝም ከአዛዦች ተራ በመሰለፋ የኔም ጀሌነት በጥቂቱም ቢሆን ተሻሻለ። የቤኒቶ አድራሻም ሆነ እንዴት እንዳለ የሚነግረን ሰው ጠፋ። ከግዜ በህዋላም እየረሳነው ሄድንና ስለሱም ማውራት ተውን። ቀስ በቀስ እያደግን ስንሄድ አድራሻ በመለወጥም ሆነ በሌላ ምክንያቶች እየተበታተንን ሄድን።
የበቀለ እብዱ ብቸኛ ኩዴታ ሙከራ በተካሄደ በሃያ አራተኛው አመት የድሮው አሮፐላን ማረፊያ ካለው አርሚ አቬሽን ቢሮዬ ውስጥ ቁጭ ብዬ ሳለሁ ጸሓፊያችን መጥቶ ሊያነጋግረኝ የሚፈልግ ሰው እንዳለ ነገረኝ። ማን እንደሆነ ስጠይቀው የኛ ክፍል አባል እንዳልሆነና ምናልባትም የአየር መከላከያ አባል ሊሆን እንደሚችል ሲነግረኝ እንዲያስገባው ነገርኩት። ወታደሩም እንደገባ ሰላምታ ሰጥቶ ቆመ። ሰላምታውን መልሼ መልኩን ሳስተውል የማውቀው መልክ እንደሆነ አእምሮዬ ነገረኝ። የት? መቼ? የሚለውን ጥያቄ እያብላላሁ እያለሁ ዐይኔን ትኩር ብሎ እያየ ፈገግ አለ። የጥርሱም አደራደር ሌላ ምልክት ለአእምሮዬ አስተላለፈ። ቤኒቶ! ግን ምን እንደዚህ ጠይም አደረገው? ቁመቱስ ምነው አጠረ? የሚሉት ጥያቄዎች ቢረብሹኝም ከተቀመጥኩበት ብድግ ብዬ< ቤኒቶ ነህ?> ብዬ ስጠይቀው እየሳቀ በአዎንታ እራሱን ነቀነቀ። ተቃቀፍን። ለቀቅሁትና መልኩን ደግሜ አየሁት፤ደግሜ እቅፌ አስገባሁት። ድሮ በጣም ሰውነተ ደልዳላና ረጅም ቁመና ያለው ይመስለኝ የነበረ ቤኒቶ አጭር ሰው ነው ለካ። ድሮ እንደፈረንጅ ሲበዛ ቀይ ነበር። ዛሬ ጠይም የቆዳ ቀለም ነው ያለው። እማረገውም እምለውም ጠፋኝ። ከውስጤ የደስታ ስሜት ይፈነቅለኝ ገባ። ምንም ቢሆን ግዜ ተለዋውጦ ሁኔታዎች የተገላቢጦሽ ቢሆኑም የልጅነት አለቃዬን ጥሩ አቀባበል ማድረግ ነበረብኝ። ወንበር ስቤ አስቀመጥኩትና ወንበሬ ላይ ሄጄ ቁጭ አልኩ። ለእንግዳዬ ቡና አዘዝኩለት። በመጀመሪያ የጠየቀኝ ታላቅ ወንድሜን ነበር። እየተቀባበልን ጥያቄዎችን ተወራወርን። ያሉትንና በሞት የተለዩትን ዘመዶቻችንን እንዲሁም ጓደኞቻችንን ካወሳን በህዋላ ከተለያየን ግዜ ጀምሮ ያለውን የህይወት ታሪኩን እንዲነግረኝ ጠይቄው በዝርዝር ነገረኝ። የህይወቱን ውጣ ውረድ፤ አቀበትና ቁልቁለቱን፤ ሜዳና ሸለቆውን አስዳሰሰኝ። ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈልግም። ብዙ የህይወት መመሰቃቀል ደርሶበታል። በሃይለኛነቱና በዕውቀቱ ወደር የማይገኝለት የነበረው አለቃዬ ምንም መስናክል ይበግረዋል ብዬ አላስብም ነበር። ለካስ የልጅነት አዕምሮዋችን በገርነት የሚያስበው ነበር። አለቃዬም እንደማንኛውም ሰው የተሸነፈበት የህይወት ጎዳና ነበር።
አዘንኩ፤ ግራም ተጋባሁ። ምን እንደምረዳው ስጠይቀው ከሰራዊቱ ውስጥ መልቀቅ እንደሚፈልግ አስረዳኝ። እንድረዳውም ተማጸነኝ። ይህን ለማድረግ ምን አቅም አለኝ ብለህ ነው ብዬ ስጠይቀው አለቃው የኔ ጓደኛ እንደሆነ ሲነግረኝ ምን ያህል የቤት ስራውን ሰርቶ እንደመጣ ተረዳሁ። ጓደኛዬን ተማጠንኩ፤ ቅር ቢለውም እንዲህ አይነት ጥያቄ እንዲሁ እንደማላቀርብ ስለሚያውቅ ዝርዝር ሁኔታውን ንገረኝ ብሎ ሳያስጨንቀኝ ቤኒቶን ከሰራዊቱ እንዲሰናበት ረዳኝ። የልጅነት አለቃዬን ለአንድ ወር ካየሁት በህዋላ እንደገና የውሃ ሽታ ሆነብኝ። እስከዛሬ ስለሱ ሹክ የምትለኝ ወፍ አጣሁ።